# የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምዝገባ ለ2026



ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ትምህርት መጀመር ለህጻናት፥ ለወላጆችና ለተንከባካቢዎች ኣስደሳች ጊዜ ነው። የምዝገባው ሂደት በተቻለ መጠን በቀላሉ የሚያልቅ እንዲሆን እንፈልጋለን።

በቪክቶሪያ ውስጥ፣ *በትምህርት እና ስልጠና ማሻሻያ ህግ 2006* መሰረት ልጅዎ በተሰየመው የአጎራባች ትምህርት ቤት (የእርስዎ 'የአካባቢ ትምህርት ቤት') የመማር መብት አለው።

እንዲሁም የአካባቢዎ ትምህርት ቤት ባልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ ለማስተማር ቦታ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። ትምህርት ቤቱ ማመልከቻዎን በምደባ መመሪያው መሰረት ይመለከታል። ስለ ምደባ ፖሊሲ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ በትምህርት ቤት መመዝገብ (Enrolling in school) የሚለውን ገጽ ይመልከቱ።

## የፋውንዴሽን (መሰናዶ) አዲስ ግዛት አቀፍ የጊዜ ሰሌዳ

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ አመት ፋውንዴሽን ወይም መሰናዶ ይባላል። ሁሉም የቪክቶሪያ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲከተሉት የፋውንዴሽን የምዝገባ ሰሌዳ አውጥተናል (ገጽ 3ን ይመልከቱ)። የጊዜ ሰሌዳው አላማ ለ2026 የትምህርት አመት ልጅዎን መቼ እና እንዴት በፋውንዴሽን ማስመዝገብ እንደሚችሉ እንዲረዱ ማገዝ ነው።

## ልጄን በመጀመሪያ ዓመት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማስመዝገብ ያለብኝ መቼ ነው?

ልጅዎ ትምህርት በጀመረበት በዚያው አመት በኤፕሪል 30 ዕድሜው 5 አመት መሆን አለበት።

6 አመት ለሆናቸው ህጻናት ትምህርት ቤት መማር ግዴታ ነው።

ለ2026 የትምህርት ዘመን ልጅዎን በቪክቶሪያ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ፣ በጁላይ 25፣ 2025 ለትምህርት ቤቱ የምዝገባ ማመልከቻ ያስገቡ።

## ልጄን በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ አመት እንዴት ማስመዝገብ እችላለሁ?

ልጅዎን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ አመት ለማስመዝገብ እነዚህን እርምጃዎች ይውሰዱ፡-

1. የአከባቢዎን ትምህርት ቤት፣ ትምህርት ቤቴን ፈልግ (Find my School) በሚል ድረ ገጽ ይፈልጉ (ከዚህ በታች ይመልከቱ)።
2. የትምህርት ቤት ጉብኝት ለማስያዝ ወይም ስለ ትምህርት ቤቱ እና ስለ ምዝገባ ማመልከቻ ሂደት የበለጠ ለማወቅ የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትን ያነጋግሩ።
3. ፋውንዴሽን (መሰናዶ) የምዝገባ መረጃ ጥቅል ከፋውንዴሽን መመዝገቢያ (መሰናዶ) (Enrolling in Foundation (Prep)) ያውርዱ። ጥቅሉ ከማክሰኞ ኤፕሪል 22፣ 2025 ጀምሮ የሚገኝ ሲሆን የማመልከቻ ቅጹንም ይጨምራል። ቅጹን እንዲሞሉም ትምህርት ቤቱ የቅጹን ቅጂ ሊሰጥዎት ይችላል።
4. ለፋውንዴሽን የምዝገባ ማመልከቻ **እስከ አርብ ጁላይ 25፣ 2025 ድረስ ያስገቡ**።
5. ስለ የማመልከቻዎ ውጤት **ከሰኞ ጁላይ 28 እስከ አርብ ነሐሴ 8፣ 2025 ባለው ጊዜ ውስጥ** ማሳወቂያ ይደርስዎታል። የመግባት እድል ከተሰጥዎት፣ እድሉን **እስከ አርብ ኦገስት 22፣ 2025** መቀበል አለብዎት።
6. **በ2025 በ4ኛው ተርም ወቅት** በሚደረግ የምዝገባ መረጃ እና የሽግግር ክፍለ ጊዜዎች ላይ ይሳተፉ።
7. ልጅዎ **ከረቡዕ 28 ጃንዋሪ 2026 ጀምሮ** ፋውንዴሽን ይጀምራል።

## የአካባቢዬን ትምህርት ቤት እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ከታች ያሉትን ቅደም ተከተሎች በመከተል የአካባቢዎን ትምህርት ቤት ትምህርት ቤቴን ፈልግ (Find my School) ድህረ ገጽ ላይ ያግኙ፡-

1. findmyschool.vic.gov.au ወደ ጉግል ወይም ወደ ሌላ ማሰሻ ያስገቡ።
2. ቋሚ የመኖሪያ አድራሻዎን ''Enter your address to get started' በሚለው ስር ያስገቡ።
3. 'Enrolment year' በሚለው ስር 2026ን ይምረጡ። **ማስታወሻ፡-** የ2026 የትምህርት ቤት ዞኖች በ2025 የ1ኛው ተርም መጨረሻ ላይ ይቀርባሉ።
4. 'School type' ወይም 'የትምህርት ቤት አይነት' በሚለው ስር የመጀመሪያ ደረጃን ይምረጡ።

ከዚያም ካርታው አድራሻዎን፣ የአከባቢዎን ትምህርት ቤት እና በግራ በኩል ደግሞ የትምህርት ቤቱን አድራሻ ያሳያል። መጠቆሚያውን ወደ ታች ካንከባለሉት ወይም ስክሮል ካደረጉት ደግሞ ለአድራሻዎ ቅርብ የሆኑትን አምስቱን ትምህርት ቤቶች ያሳይዎታል።

እንዲሁም በትምህርት ቤት ስም 'ትምህርት ቤት ፈልግ/Search for school' በሚለው ስር መፈለግ ይችላሉ።

## ልጄ የአካባቢያችን ትምህርት ቤት ላልሆነ የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ማመልከት ይችላል?

አዎ፣ የአከባቢዎ ትምህርት ቤት ወዳልሆኑ ወደ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ማመልከት ይችላሉ። ትምህርት ቤቱ ማመልከቻዎን ከምደባ መመሪያው እና ካለው ቦታ ጋር በሚስማማ መልኩ ይመለከታል። ማመልከቻዎች እንዴት ቅድሚያ እንደሚሰጡ በትምህርት ቤት መመዝገብ/Enrolling in school ገጽ ላይ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## የምዝገባ ማመልከቻዬ አልተሳካም የሚል ደብዳቤ ከደረሰኝ በኋላ ምን ይሆናል?

ልጅዎን ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ማመልከት አለብዎት። ልጅዎ በአካባቢዎ ትምህርት ቤት ቦታ የማግኘት ዋስትና አለው። የልጅዎ የአካባቢ ትምህርት ቤት የሚወሰነው በቋሚ የመኖሪያ አድራሻዎ መሰረት ነው። የልጅዎን የአካባቢ ትምህርት ቤት ለማግኘት ትምህርት ቤቴን ፈልግ/Find my Schoolየሚለውን ይጎብኙ። የትምህርት ቤት መመዝገቢያ/Enrolling in school ገጽም የልጅዎን መመዝገቢያ አድራሻ ለማረጋገጥም ሊረዳዎት ይችላል።

እንዲሁም ውሳኔውን ይግባኝ ማለት ይችላሉ። የፋውንዴሽን (ዝግጅት) መመዝገቢያ/ Enrolling in Foundation (Prep) ገጽ የምዝገባ ማመልከቻ ውጤት ይግባኝ ለማለት ባለው ሂደቱ ላይ መረጃ አለው።

## የምዝገባ የጊዜ ገደቦች ካለፉብኝ ምን ይሆናል?

ልጅዎን ለ2026 የትምህርት ዘመን ፋውንዴሽን ለማስመዝገብ ከ2025 2ኛ ተርም ጀምሮ በማንኛውም ጊዜ ማመልከት ይችላሉ።

የምዝገባ ማመልከቻ እስከ አርብ ጁላይ 25፣ 2025 ድረስ እንዲያስገቡ ቢጠየቁም፣ የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ካመለጣቸው ቤተሰቦች፣ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ ከቀየሩ ወይም አዲስ ወደ ቪክቶሪያ ከመጡ ቤተሰቦች ከዚህ ቀን በኋላ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች አሁንም ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

ከጁላይ 25፣ 2025 በኋላ የሚገቡ የምዝገባ ማመልከቻዎች በመምሪያው ምደባ መመሪያ መሰረት ትምህርት ቤቱ እንደተቀበላቸው በትምህርት ቤቱ ይስተናገዳሉ።

## የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለመመዝገብ ተጨማሪ መረጃ የት ማግኘት እችላለሁ?

ስለ ፋውንዴሽን ምዝገባ ሂደት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በአካባቢዎ የሚገኘውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መጠየቅ ይችላሉ።

በ2025 2ኛ ተርም መጀመሪያ ላይ በፋውንዴሽን የምዝገባ ሂደት ላይ በፋውንዴሽን መመዝገቢያ (መሰናዶ)/Enrolling in Foundation (Prep) ገጽ ላይ የመረጃ ጥቅል ማግኘት ይችላሉ።

የመረጃ ጥቅሉን ለመተርጎም እገዛ ከፈለጉ፣ እባክዎን ለእርዳታ በአካባቢዎ የሚገኘውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

## ለእርዳታ ማንን አነጋግራለሁ?

ለማመልከት የምትፈልጉት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሽግግር አስተባባሪ፣ የምዝገባ ኦፊሰር ወይም ርእሰ መምህር ስለምዝገባ ሂደቱ ሊኖርዎት የሚችል ማንኛውም አይነት ጥያቄ ሊረዳዎት ይችላል።

## ጠቃሚ ማገናኛዎች (ሊንኮች)

ልጅዎ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሲጀምር ለእርስዎ ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ ጠቃሚ ማገናኛዎችን ከዚህ በታች ይመልከቱ፡-

ትምህርት ቤቴን ፈልግ - findmyschool.vic.gov.au

የትምህርት ቤት ዞኖች መረጃ - vic.gov.au/school-zones

በፋውንዴሽን (መሰናዶ) መመዝገብ - vic.gov.au/enrolling-foundation-prep

በትምህርት ቤት መመዝገብ – vic.gov.au/how-choose-school-and-enrol

የአካል ጉዳት እና አካታች ትምህርት - vic.gov.au/disability-and-inclusive-education

የክልል ቢሮ አድራሻዎች - vic.gov.au/office-locations-department-education

# የ2025-26 የጊዜ ሰሌዳ

| የ 2025 ቀናት | ተግባራዊ እንቅስቃሴ |
|---|---|
| **2ኛ ተርም፡- ማክሰኞ አፕሪል 22፣ 2025 – ዓርብ ጁላይ 4፣ 2025** | |
| **የ2025 1ኛ እና 2ኛ ተርሞች** | የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለ2026 ለልጃቸው ፋውንዴሽን (መሰናዶ) ምዝገባ ለሚፈልጉ ቤተሰቦች ጉብኝቶችን፣ የመረጃ ክፍለ ጊዜዎችን እና ሌሎች ተግባራትን ያካሂዳሉ። |
| **በ2025 የ2ኛ ተርም መጀመሪያ ላይ** | የ2026 የትምህርት ዘመን የትምህርት ዞኖች በ findmyschool.vic.gov.au ላይ በቀጥታ ይለቀቃሉ<br>ወላጆች እና ተንከባካቢዎች ለ2026 የተመደበላቸውን የሰፈር ትምህርት ቤት (የአካባቢ ትምህርት ቤት) ለማግኘት ወደ findmyschool.vic.gov.au መድረስ አለባቸው።<br>ለወላጆች እና ተንከባካቢዎች የተዘጋጀ የምዝገባ መረጃ ጥቅል ከመመዝገቢያ ፋውንዴሽን (መሰናዶ)/Enrolling in Foundation (Prep) ማውረድ ይቻላል። |
| **ከ2025 2ኛ ተርም የመጀመሪያ ሳምንት ጀምሮ** | የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የምዝገባ መረጃ ፓኬጆችን ለዕጩ ቤተሰቦች እና ለአካባቢያቸው ማህበረሰብ ሊያከፋፍሉ ይችላሉ። |
| **ከ2025 2ኛ ተርም የመጀመሪያ ሳምንት ጀምሮ** | **የምዝገባ ማመልከቻዎች ክፍት ይሆናሉ** - ወላጆች እና ተንከባካቢዎች ከዚህ ቀን ጀምሮ የተጠናቀቁትን የምዝገባ ማመልከቻዎቻቸውን ለመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ያስገባሉ። |
| **3ኛ ተርም፡- ሰኞ ጁላይ 21፣ 2025 – ዓርብ ሴፕተምበር 19፣ 2025** | |
| **ዓርብ ጁላይ 25፣ 2025** | **የምዝገባ ማመልከቻዎች የመጨረሻ ቀን** - ወላጆች እና ተንከባካቢዎች በዚህ ቀን የተጠናቀቁትን የምዝገባ ማመልከቻዎቻቸውን ለመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ያቀርባሉ። |
| **በሰኞ ጁላይ 28 እና ዓርብ ኦገስት 8፣ 2025 መሃከል** | አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመምሪያው የምደባ ፖሊሲ መሰረት ለወላጆች እና ተንከባካቢዎች የፋውንዴሽን (መሰናዶ) ምዝገባ ውጤቶችን በጽሁፍ ያሳውቃሉ። ይህ መቀበልን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ፣ ምዝገባን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ወይም ያልተሳካ ማመልከቻ ምላሽ ደብዳቤን ሊያካትት ይችላል።<br>ያልተሳካ ማመልከቻ ምላሽ ደብዳቤ የደረሳቸው ወላጆች እና ተንከባካቢዎች ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የይግባኝ ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ ሊጀምሩ ይችላሉ። |
| **አርብ ኦገስት 22፣ 2025** | መቀበልን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ የደረሳቸው ወላጆች እና ተንከባካቢዎች የልጃቸውን ቦታ መቀበላቸውን እስከዚህ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ይሰጣሉ። |
| **አርብ ኦገስት 22፣ 2025** | ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወላጆች እና ተንከባካቢዎች በጽሁፍ ይግባኝ ማቅረብ **የሚዘጋበት ቀን**። |
| **ዓርብ ሴፕተምበር 5፣ 2025** | የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የይግባኝ ማመልከቻ ውጤት እስከዚህ ቀን ድረስ ለሁሉም ወላጆች እና ተንከባካቢዎች በጽሁፍ ያሳውቃሉ። |
| **ዓርብ ሴፕተምበር 19፣ 2025** | ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ያልተሳካላቸው ወላጆች እና ተንከባካቢዎች ለሚመለከተው የክልል ዳይሬክተር በጽሁፍ ይግባኝ ማቅረብ **የሚዘጋበት ቀን**። |
| **4ኛ ተርም፡- ሰኞ ኦክቶበር 6 – ዓርብ ዲሰምበር 19፣ 2025** | |
| **በ2025 4ኛ ተርም ወቅት** | የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሽግግር ክፍለ ጊዜዎችን ያስተናግዳሉ። |
| **ዓርብ ኦክቶበር 31፣ 2025** | ክልሎች የክልል ዳይሬክተር የይግባኝ ውጤት እስከዚህ ቀን ድረስ ለሁሉም ወላጆች እና ተንከባካቢዎች በጽሁፍ ያሳውቃሉ። ይህ የሚመለከተው ዓርብ ሴፕቴምበር 19፣ 2025 እስከ መዝጊያው ቀን ድረስ ለተቀበልዋቸው ይግባኞች ብቻ ነው። |